- ሕዝቡ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ለስጋቸው ስለሚያስፈልጋቸው ምግብ መሰላቸው።

- ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ለሥጋቸው ስለሚያስፈልጋቸው እንጀራ ነበር?

- አይደለም።

- ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ መንፈሳዊ እንጀራ ነበር።

ዮሐንስ 6፡35

35- ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፤ በእኔም የሚያምን ፈጽሞ አይጠማም።»

- ኢየሱስ እርሱ ከሰማይ የወረደ መንፈሳዊ እንጀራ መሆኑን ተናገረ።

- አንድ ሰው ምግብ ካልበላ ይሞታል?

- አዎን።

- ሰዎች ምግብ ካልበሉ እንደሚሞቱ ሁሉ ለመንፈሳችን ብቸኛ ምግብ በሆነው በኢየሱስ ካላመንን እኛም እንሞታለን።

- በኢየሱስ ካመንን መንፈሳችን ፈጽሞ ዳግም አይራብም።



## ትምህርት 57

1. ኢየሱስ ለምን ደከመ?

ሀ- ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ አምላክ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ሰው ስለነበር ነው።

2. ኢየሱስ ነፋሱንና ባሕሩን ጸጥ እንዲሉ ማዘዝ የቻለው እንዴት ነው?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ ነው።

3. ነፋሱና ባሕሩ ለኢየሱስ የታዘዙት ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም ነፋሱንና ባሕሩን የፈጠራቸው ኢየሱስ ስለሆነ ነው።

4. በአጋንንት የተያዘው ሰው በቁጥጥራቸው ሥር ካዋሉት ከአጋንንት ሁሉ ኃይል ራሱን ማዳን ችሎ ነበር?

ሀ- አልቻለም።

5. ሌሎች ሰዎችስ ይህን ሰው በቁጥጥራቸው ሥር ካዋሉት ከአጋንንት ኃይል ሊያድኑት ችለዋል?

ሀ- አልቻሉም።

6. አጋንንት ሰዎችን እንደሚጠሉ በምን እናውቃለን?

ሀ- አጋንንት ይህን ሰው ሰዎች በሚቀበሩበት ዋሻ ውስጥ እንዲኖር በማስገደዳቸው።

ለ- አጋንንት ይህ ሰው የራሱን አካል እንዲቆራርጥ በማድረጋቸው።

7. የአጋንንት ሁሉ አለቃ ማን ነው?

ሀ- ሰይጣን።

8. ከሰይጣን፥ ከአጋንንቱም የሚበልጠው ማን ነው?

ሀ- ኢየሱስ፤ እርሱም እግዚአብሔር።

9. ዓሣማዎቹ በሙሉ ሲሞቱ አጋንንቱ ያልሞቱት ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም አጋንንት መናፍስት ናቸው።

ለ- ምክንያቱም አጋንንት እንደ ሰዎችና እንስሳት ያለ አካል ስለየሌላቸው ነው።

10. ሰውየውን ከአጋንንት እሥራት ነፃ ያወጣው ማን ነው?

ሀ- ኢየሱስ።

- ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ራቅ ወዳለው የገሊላ ባሕር ዳርቻ ሄዱ።

ዮሐንስ 6፡1-2

1- ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ጥብርያዶስ የተባለውን የገሊላ ባሕር ተሻግሮ ራቅ ወዳለው የባሕሩ ዳርቻ ሄደ።

2- ብዙ ሰዎችም በሽተኞችን በመፈወስ ያደረጋቸውን ታምራዊ ምልክቶች ስላዩ ተከተሉት።

- ብዙ ሕዝብ ኢየሱስን የተከተለው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ሕዝቡ ኢየሱስ በበሽተኞች ላይ የሚያደርጋቸውን ተአምራዊ ምልክቶች ለማየት ስለፈለጉ ነው።

ዮሐንስ 6፡3

3- ከዚያም ኢየሱስ ወደ ተራራ ወጥቶ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ።



- ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ በምድረ በዳ ለእስራኤላውያን ከሰማይ እንጀራ እንደ ሰጣቸው ሁሉ እግዚአብሔር አብ ከሰማይ እውነተኛውን እንጀራ እንደሚሰጣቸው ነገራቸው።

- እግዚአብሔር አብ ለሰዎች የሚሰጠው ከሰማይ የመጣ እውነተኛ እንጀራ ማን ነው?

- ኢየሱስ ነው።

- ኢየሱስ እግዚአብሔር በምድረ በዳ ለእስራኤላውያን ከሰጣቸው መና ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነበር?

- መና ከሰማይ እንደ ወረደ ሁሉ ኢየሱስም ከሰማይ በመውረዱ።

- መና የተሰጠው በእግዚአብሔር እንደ ሆነ ሁሉ ኢየሱስም ከእግዚአብሔር የተሰጠ በመሆኑ።

- እስራኤላውያን መናውን ካልበሉ እንደሚሞቱ ሁሉ ሰዎች በኢየሱስ ካላመኑ የሚሞቱ በመሆናቸው።

- ሕዝቡ ኢየሱስ የተናገረውን ተረድተዋል?

ዮሐንስ 6፡34

34- እነርሱም፣ «ጌታ፣ እንግዲያውስ ይህን እንጀራ ሁልጊዜ ስጠን» አሉት።

- ሕዝቡ ኢየሱስ የተናገረውን አልተረዱም።

30- ስለዚህ እንዲህ ብለው ጠየቁት፣ «አይተን እንድናምንህ ምን ታምራዊ ምልክት ታደርጋለህ? ምንስ ትሠራለህ?

31-‘ይበሉ ዘንድ ከሰማይ እንጀራን ሰጣቸው’ ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ።»

- ሕዝቡ ሙሴ ለእስራኤላውያን በየዕለቱ መና እንደሰጣቸው ሁሉ ኢየሱስም በየዕለቱ እንጀራ እንዲሰጣቸው እንደሚፈልጉ ነገሩት።

- ኢየሱስ ምን መለሰላቸው?

ዮሐንስ 6፡32-33

32- ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «እውነት እላችኋለሁ፤ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም፤ እውነተኛውን እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ ግን አባቴ ነው፤

33- የእግዚአብሔር እንጀራ እርሱ ከሰማይ የሚወርድ፣ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና።»

- በምድረ በዳ ለእስራኤላውያን እንጀራ የሰጣቸው ሙሴ ነው?

- አይደለም።

- በምድረ በዳ ለእስራኤላውያን እንጀራ የሰጣቸው ማን ነበር?

- እግዚአብሔር።

- ኢየሱስ በምድረ በዳ ለእስራኤላውያን እንጀራን የሰጠው እግዚአብሔር አብ ነው አለ።



- ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ተራራ ቢወጡም እጅግ ብዙ ሕዝብ ተከተላቸው።

- ሕዝቡ ብዙ በመሆኑ ቁጥሩ ከአምስት ሺህ በላይ ነበር።

- ከዚያም ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የሆነውን ፊልጶስን አንድ ጥያቄ ጠየቀው።

ዮሐንስ 6፡5-7

5- ኢየሱስም ቀና ብሎ ሲመለከት ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ ሲመጣ አየ፤ ፊልጶስንም፣ «እነዚህ ሰዎች እንዲበሉ እንጀራ ከየት እንግዛ?» አለው።

6- ይህን የጠየቀው ሊፈትነው እንጂ ራሱ ሊያደርግ ያሰበውን ያውቅ ነበር።

7- ፊልጶስም፣ «እያንዳንዱ ሰው ትንሽ ትንሽ እንዲቃመስ ለማድረግ፣ የሁለት መቶ ዲናር እንጀራ እንኳ አይበቃም» ሲል መለሰ።

- ኢየሱስ ፊልጶስን ይህን ጥያቄ የጠየቀው ለምን ነበር?

- ኢየሱስ ሊያደርግ ያሰበውን እያወቀ ይህንን የጠየቀው ፊልጶስን ሊፈትነው ፈልጎ ነው።

ዮሐንስ 6፡8-9

8- ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፣ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስም፣ እንዲህ አለ፤

9- «አምስት ትንንሽ የገብስ እንጀራና ሁለት ትንንሽ ዓሣ የያዘ አንድ

ልጅ እዚህ አለ፤ ይህ ግን ለዚህ ሁሉ ሕዝብ እንዴት ይዳረሳል?» አለ።

- የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ይህን ሁሉ ሕዝብ እንዴት መመገብ እንዳለባቸው አላወቁም።

- ኢየሱስ ያላቸው እንዲህ ነው።

ዮሐንስ 6፡10-13

10- ኢየሱስም፣ ሰዎቹ እንዲቀመጡ አድርጉ» አለ። በዚያ ቦታ ብዙ ሣር ነበረ፤ አምስት ሺህ ያህል ወንዶችም ተቀመጡ።

11- ኢየሱስ አምስቱን እንጀራ አንሥቶ አመሰገነ፤ ለተቀመጡትም የሚፈልጉትን ያህል ዐደለ፤ ዓሣውንም እንዲሁ።

12- ሁሉም በልተው ከጠገቡ በኋላ፣ ደቀ መዛሙርቱን፣ «ከተረፈው ቍርስራሽ ምንም እንዳይባክን ሰብስቡ» አላቸው።

13- እነርሱም፣ ከተበላው አምስት የገብስ እንጀራ የተረፈውን ቍርሽራሽ ሰብስበው ዐሥራ ሁለት መሶብ ሞሉ።

- ኢየሱስ እግዚአብሔር አብን ካመሰገነ በኋላ እንጀራውንና አሣውን ቆርሶ ደቀ መዛሙርቱ ለሕዝቡ እንዲያከፋፍሉ ሰጣቸው።

- ኢየሱስ ሕዝቡን መመገብ ሲጀምር ስንት እንጀራና ስንት ዓሣ ነበረው?

- አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ።

- በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ ኢየሱስ ስንት ሰዎችን መገበ?

- ከአምስት ሺህ ሕዝብ በላይ።



- ኢየሱስ ለመንፈሳዊ ምግባችን መሥራት ለሥጋዊ ምግባችን ከመሥራት የበለጠ አስፈላጊ ነው ማለቱ ነበር።

- ልንሠራ የሚገባው መንፈሳዊ ምግብ ምንድን ነው?
- የእግዚአብሔር ቃል።

- ቀጥሎም ሕዝቡ ኢየሱስን ጠየቀው።

ዮሐንስ 6፡28-29

28- እነርሱም፣ «ታዲያ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ምን ማድረግ አለብን?» አሉት።

29- ኢየሱስም፣ «እርሱ በላከው ታምኑ ዘንድ፣ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው» ሲል መለሰላቸው።

- ሕዝቡ ኢየሱስን የጠየቁት ምን ነበር?

- ሕዝቡ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ምን መሥራት እንዳለባቸው ጠየቁት።

- የኢየሱስ መልስ ምን ነበር?

- ኢየሱስ እግዚአብሔርን የሚያስደሰት ሥራ በኢየሱስ ማመን ብቻ መሆኑን ነገራቸው።

- ሕዝቡ ኢየሱስ የነገራቸውን ተቀብለው ነበር?
- አልተቀበሉም።

ዮሐንስ 6፡30-31

- አዎን።

- ኢየሱስ ሕዝቡን ምን አላቸው?

ዮሐንስ 6፡26-27

26- ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «እውነት እላችኋለሁ የምትፈልጉኝ እንጀራ ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ እንጂ፣ ታምራዊ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም።

27- ለሚጠፋ እንጀራ አትሥሩ፤ ነገር ግን የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር ምግብ ሥሩ፤ ለዚህም እግዚአብሔር አብ ማረጋገጫ ማኅተሙን በእርሱ ላይ አትሞአልና።»

- ኢየሱስ ሕዝቡ የፈለጉት እንጀራ ስለ ሰጣቸው ብቻ መሆኑን ተናገረ።

- ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አለ፡-

- «ለሚጠፋ እንጀራ አትሥሩ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር ምግብ ሥሩ» አላቸው።

- ኢየሱስ ለዕለት እንጀራችን ሥራ መሥራት ስሕተት ነው ማለቱ ነበር?

- አይደለም።

- እኛ ሁላችንም የዕለት ምግብ ለማግኘት መሥራት አለብን።

- ታዲያ ኢየሱስ ምን ማለቱ ነበር?

- ኢየሱስ ስለ መንፈሳዊ ምግባችን ማሰቡ ለሥጋዊ ምግባችን ከማሰቡ የበለጠ አስፈላጊ ነው ማለቱ ነበር።



- ኢየሱስ በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ ከአምስት ሺህ ሕዝብ በላይ እንዴት ሊመግብ ቻለ?

- ምክንያቱም ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ።

- ምክንያቱም ኢየሱስ ማናቸውንም ነገር ማድረግ ስለሚችል።

- ሰዎቹ ሁሉ ከበሉ በኋላ ምን አሉ?

ዮሐንስ 6፡14-15

14- ሰዎቹም ኢየሱስ ያደረገውን ታምራዊ ምልክት ካዩ በኋላ፣ «ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ በእርግጥ ይህ ነው» አሉ።

15- ኢየሱስም ሰዎቹ መጥተው በግድ ሊያነግሡት እንዳሰቡ ዐውቆ እንደ ገና ብቻውን ወደ ተራራ ገለል አለ።

- ሕዝቡ ኢየሱስን ለማንገሥ የፈለጉት ለምን ነበር?

- ኢየሱስ ሁልጊዜ እንጀራ እንዲሰጣቸው ስለ ፈለጉ።

- ሕዝቡ ኢየሱስ ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን እንዲያድናቸው ፈልገው ነበር?

- አልፈለጉም።

- ለሆዳቸው ብቻ ያሰቡ ነበር።

- ኢየሱስ በሕዝቡ ላይ መንገሥ ያልፈለገው ለምን ነበር?

- ኢየሱስ የሰዎቹ ልብ ክፉ መሆኑን ስለሚያውቅ ነበር።

- ኢየሱስ ሕዝቡ ሊያነግሡት የፈለጉት እንጀራ እንዲሰጣቸው ስለፈለጉ ብቻ መሆኑን ያውቅ ስለነበር።

- ከሕዝቡ የተነሣ ኢየሱስ ወደ ሌላ ቦታ ሄደ።

- በመሸም ጊዜ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በጀልባ ተሳፍረው የገሊላ ባሕርን ማቋረጥ ጀመሩ።

ዮሐንስ 6፡16-21

16- በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ባሕር ወረዱ፤
17- በጀልባውም ተሳፍረው ወደ ቅፍርናሆም ለመሻገር ተነሡ።
ጊዜው መሽቶ ነበር፤ ኢየሱስም ወደ እነርሱ ገና አልመጣም ነበር።
18- ኀይለኛ ነፋስ ይነፍስ ስለ ነበር ባሕሩ ተናወጠ።
19- አምስት ወይም ስድስት ኪሎ ሜትር ያህል እንደ ቀዘፉ፣
ኢየሱስ በውሃ ላይ እየተራመደ ወደ ጀልባዋ ሲመጣ አይተው ደነገጡ።
20- እርሱ ግን፣ «እኔ ነኝ፤ አትፍሩ» አላቸው።
21- እነርሱም እንዲሳፈር ፈለጉ፤ ጀልባዋም ወዲያውኑ
ወደሚሄዱበት ዳርቻ ደረሰች።

- ደቀ መዛሙርቱ ለምን ፈሩ?

- ኢየሱስ በባሕሩ ላይ እየተራመደ ወደ እነርሱ ሲመጣ በመመልከታቸው ነው።



- በውኃ ላይ መራመድ የሚችል ሰው አለ?

- የለም።

- በውኃ ላይ መራመድ የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው።

- እንደ ኢየሱስ ያለ ማንም የለም።

- ኢየሱስ ባሕሩን ስለ ፈጠረ በባሕሩ ላይ መራመድ ይችላል።

- ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ የፈለገውን ማናቸውንም ነገር ማድረግ ይችላል።

- በኋላም ሕዝቡ ኢየሱስን ፍለጋ ሄዱ።

ዮሐንስ 6፡22-25

22- በማግሥቱ በባሕሩ ማዶ የቀሩት ሰዎች በዚያ አንዲት ጀልባ ብቻ እንደ ነበረች ተረዱ፤ ኢየሱስ እንዳልተሳፈረና ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን እንደ ሄዱም ዐወቁ።

23- ከዚያም በኋላ፣ ሌሎች ጀልባዎች ከጥብርያዶስ፣ ሕዝቡ ጌታ የባረከውን እንጀራ ወደ በሉት ስፍራ መጡ፤

24- ሰዎቹም፣ ኢየሱስ ወይም ደቀ መዛሙርቱ በዚያ አለመኖራቸውን እንዳወቁ፣ ኢየሱስን ፍለጋ በጀልባዎቹ ወደ ቅፍርናሆም ሄዱ።

25- ከባሕሩ ማዶ ባገኙትም ጊዜ፣ «ረቢ፣ መቼ ወደዚህ መጣህ?» አሉት።

- ሕዝቡ ኢየሱስን የፈለጉት ለምን ነበር?

- ኢየሱስ ተጨማሪ ምግብ እንዲሰጣቸው ስለ ፈለጉ?

- ኢየሱስ ሕዝቡ የሚከተለው ለምን እንደ ሆነ ያውቅ ነበር?